# ጋዜጣዊ መግለጫ



የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2014/44*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለሶማሌ ክልል ለግመልና ለላም ወተት መሰብሰቢያና ማቀነባበሪያ የሚውል የ350,000 ዶላር የገንዘብ እርዳታ አደረገ

*3,000 የሚሆኑ የአርብቶ አደር አባወራዎች ዘላቂነት ላለው የወተት ገበያ ከሚኖራቸው ተደራሽነት ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል*

**ጅጅጋ፤ሶማሌ ክልል፤ህዳር 9 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-** የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር የአርብቶ አደሩን የወተት ገበያ ለማሻሻልና አጠቃላይ በሀገሪቱ በዘርፉ ያሉትን አቅራቢዎች ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በጅጅጋ ከተማ ለሚገኘው በራዋኮ የወተት ማቀነባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ የ350,000 ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸውን አስታወቁ፡፡

በራዋኮ የወተት ማቀነባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በቅርቡ የላምና የግመል ወተት አቀነባብሮ የተለያዩ የወተት ተዋጽኦዎችን ለማቅረብ የተቋቋመ ሲሆን፤የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ ለኩባንያው ያደረገው ድጋፍ በዱሁሻ፣ፋፋን፣ቦምባስ፣ባቢሌ፣አውባሬና ቀብሪበያህ የሚኖሩ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አባወራዎች አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የወተት ገበያ እንዲያገኙ የሚያስችል ይሆናል፡፡ የተሻለ የገበያ ተደራሽነት መኖሩም የወተት ምርትንና አጠቃላይ በዘርፉ ያለውን የእንስሳት ምርታማነት ያሳድጋል፡፡ ኩባንያው በሂደት ምርቶቹን ወደ ጅቡቲና ሶማሊላንድ እንደሚልክም ታውቋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የማጠናከርና ገበያን የማስፋፋት መርሀ ግብር የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመቀየር ከሚሠሩ ከተለያዩ የንግድ ተቋማት ጋር በትብብር የሚሠራ ነው፡፡ የኤጀንሲው ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር በቦታው ተገኝተው የገንዘብ ድጋፍ መደረጉን ባሳወቁበት ወቅት ሲናገሩ፡-“ዓላማችን ለወተት አምራቾች የተሻሻለ አመጋገብን፣የሥራ ዕድሎችንና የተሻለ ገቢ መፍጠር ሲሆን፤ ይህም ከኢትዮጵያ መንግሥት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው” ብለዋል፡፡

ለበራዋኮ የወተት ማቀናባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ  የተደረገው የገንዘብ ድጋፍ የተገኘው ኤጀንሲው የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የማጠናከርና ገበያን የማስፋፋት መርሀ ግብር በኩል የሚስተዳድረው የልዩ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሲሆን፤ አሸናፊው የሚመረጠው ተወዳዳሪዎች በግብርና ምርት ንግድ ላይ ተሰማርተው የአርሶ አደሩንና የከፊል አርሶ አደሩን ማህበረሰብ ገቢ በማሳደግ ዙሪያ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው፡፡ የማቀነባበሪያ ፋብሪካው ባለቤት አሚር ሙክታር ስለተደረገው ድጋፍ በተናገሩበት ወቅት፡- “የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የማጠናከርና ገበያን የማስፋፋት መርሀ ግብር ህልሜ እውን እንዲሆን ረድቶኛል” ሲሉ አመስግነዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የማጠናከርና ገበያን የማስፋፋት መርሀ ግብር ለበራዋኮ ያደረገው ድጋፍ የላምና የግመል ወተትን የመግዛት አቅምን በማጠናከር ላይ ያተኮረና ኩባንያው ከ3000 በላይ ከሚሆኑ የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አባወራዎች ወተት

በመረከብ በቀን ከ15,000 ሊትር የሚልቅ ወተት አቀነባብሮ ማምረት የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። መርሀ ግብሩ በየደረጃው ያሉ በማቅረብ ሥራው ላይ ለተሠማሩ የየአካባቢው የአምራቾችና የሴቶች ቡድኖች፣ወተት ሰብሳቢዎችና ነጋዴዎች፣አቀነባባሪዎችና የሽርክና ማህበራቶቻቸው የሚጠበቅባቸውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉና በሥራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል።

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የማጠናከርና ገበያን የማስፋፋት መርሀ ግብር ከ2004-2009 ዓ.ም. የሚተገበር የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ሲሆን፤የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው መጪውን ትውልድ መመገብ ከተሰኘ በአፋር፣በሶማሌና ኦሮሚያ ክልሎች ባሉ ቆላማ አካባቢዎች የሚኖሩ አባወራዎችን ገቢ ማሳደግና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚችሉበትን ቅንጅት የሚፈጥር የአሜሪካ መንግሥት ፕሮግራም ነው።

###